01.08.11

ማመልከቻ ለመንግሥተ እግዚአብሔር

<u>ክቡር ሆይ</u>

ለቀጣዩ ዓቤቱታዬ ፈጣን መልስ ባገኝ ምኞቴና ጸሎቴ ነው፡፡ ባላሰብኩትና በተወጠርኩበት ጊዜ አባባ ኤርምያስ ካጣብቂኝ ውስጥ አስገብተኛል፡፡ አመክንዮቴንም እነሆ፤

ሀ. አባቴ ሆይ የማዕረግ ስምን በተመለከተ ልክ ርእስዎ ለእኔዎቹ ቃሎች ምክንያት እንደሠጡኝ ሁሉ አሁን ምክንያቴን ለማቅረብ ባልችልም ርእስዎ የሚፈልጓቸዉን ስያሜዎች በተቀብያነት ላለመቀጠል ግላዊ መብት እንዳለኝ ይቀበሉ ዘንዳ በትኅትና እጠይቃለሁ፡፡

ለ. ሥነፊደላቱ ግን ብዙ እና እጅግ ብዙ ምሥጢሮች ያልሉባቸዉ መሆኑን አስተምረኛል፡፡ ግን ስለተውላጠ ፊደሎች ማዎቅም ሆነ መግገለፅ ያልለበት በዚሁ መንገድ በኩል ይችቻላል ወይ? አይመስለኝም! ይሆናል ካሉ ለሚከተሉቱ ጥያቄዎቼ መልሱን እሻለሁ!

ምሳሌ ሠጠ፤ ለገሠ- አበረከተ- መፀዎተ

ሰጠ፤ ተቀማ- ተዘረፈ- ተነጠቀ

ሠረቀ፤ በረቀ-ፈለቀ- አንፀባረቀ

ሰረቀ፤ ቀማ- ነጠቀ…

ፊደሎቻችን ለእየራሳቸዉ ግላዊ ትርጓሜ አላቸዉ እንጅ ከቃላቱ ጋራ ብቻ የተቆራኙ አደልሉም! ስላልሆነም ነው እኮ፤

ተነሣ ብሎ መነሻ፤ ደረሰ ብሎም መድረሻ፤ ጨረሰ ይልና መጨረሻ ወዘተ. የሚለው፡፡

ሐ. አዎ ዕውቀት በጥረት ይግገኛል፡፡ ጥበብን ግን መምማር የግድ ነው፤ በምኞት አይግገኝም፡፡ ርእስዎ የሚሏቸቸዉ ምሥጢሮች ሁሉ በሀረጋችን ነበሩ-አሉ፡፡ ግን በሥሜታዊ ምክንያት ሳይሆን በተጨባጩ ነው እንጅ፡፡ ለዚሁ ምሳሌ ይሆን ዘንዳ እስኪ የሚክከተለውን ይተቹበት፡፡

መልካሙን ሁሉ እመኝልዎታለሁ

ልጅዎ

ዳዊት

------------------------------------------------------------------------------------------

ለምሳሌ <u>ለእምነት እና ሃይማኖት ግብራቸዉ</u>:- ተስፋ -ጽድቅ እና ዘለዓለማዊነት፣ <u>ባህርያቸዉ</u> ደግሞ መኖር -ኑሮ እና ሕይዎት /ልደት-ዕድገት-ሞት/፣ <u>ምንጫቸዉም</u> እንዲሁ ፍጥረት- ተፈጥሮ- ፍጡር እና ፈጣሪ -መለኮት ሲሆን ከዚሁ ላይ በመምመሥረትና በመንነሣት ደግሞ መለኮት እና አምላክ፣ አማልክት እና ነገደ መላእክት፣ አጋዕዝትና ኃይላት፣ ጻድቃንና ሰማዕታት፣ ነቢያት እና ሐዋርያት፣ ቅዱሳንና ምእመናን፣ ወዘተ. ስለሚብባሉቱ ባህርያት ማስተማር አልለብኝ::

----

ለምሳሌ ለእምነት መሠረታዊ ባህርያቱ ናቸዉ ብለዉ አባቶቻችን እንዳስተማሩን ሁሉ፣-

<u>ለመለኮት- ፈጣሪ- አምላክ ግብሩ</u> እነሆ ጥንተዓለም ተፈጥሮን- ዓለምን- ፍጥረታትን ካለመኖር ወደመኖር ማምጣት፣ ድኅረዓለም /ከዓለም በኋላ/ ደግሞ ዓለማትን -ፍጥረታትን -ተፈጥሮን እንደገና መልሶ ከመኖር ወደአለመኖር መውሰድ፣ መዓልትንና ሌሊትን መቀያየር እናም እንዲሁ ክረምትንና በጋንም ማፈራረቅ፣ ወዘተ. የሚሉትንና የመሳሰሉን የሚያካትት ሲሆን፣

<u>ባህርዩ</u> ደግሞ መሥጠትና መንሳት፣ መግደልና ማዳን፣ መዓትና ምኅረት፣ ቁጥዓና ትዕግሥት፣ ወዘተ. የሚሉትንና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል::

<u>ምንጩም</u> እንዲሁ አንድነት እና ዋሕድነት፣ ጥንተቀደምትነት- ቀዳሚነት እና መጀመሪያ- መንነሻአልባት፣ ሥፋት እና ምልዓት፣ ርቅቀት /ረቀቀ/ እና ምጥቀት፣ ኗሪነት-ሕያዊነት እና ቋሚነት፣ ፍጹምነት እና ምሉዕነት፣ ዘለዓለማዊነት እና ፍጻሜ -መጨረሻአልባነት፣ ወዘተ. የሚሉትንና የመሳሰሉትን ይይዛል::

ምንጩን ግን ከዚሁ ላይ ማለፍ ፈልጌ ነበረ:: ምክንያቱም እኔ በቃሌ ከማስታውሰውና ከማውቀው ይልቅ እጅጉን በይበልጥ ባለፈው ጊዜ ከተረጎምነው የመምህር አባሞን ጽሑፍ ውስጥ በትክክልና በሚገባ

ተብራርቶ ስለተቀመጠ ያንኑ ፈልጌ ከዚሁ ላይ ለማስቀመጥ አሁን ጊዜ የልለኝም እንጅ።

--------------እስኪ ትንሽ ልጨምርበት-----------

<u>**ለመለኮት- አምላክ ግብሩ**</u> እነሆ ፍጥረታትን ካለመኖር ወደመኖር ማምጣት እና እንደገና መልሶ ከመኖር ወደአለመኖር መውሰድ ማለቱሳ ፍጥረታት ሁሉ አልነበሩምና አይኖሩም ለማለት ነውን? ቢሉሳ!

ዓይ ይህማ እንዴትና እንደምን ሁኖ!? ፈጣሪ የሚትታዎቀው በፍጥረታቱ ዓማካይነት እና የፍጥረታቱን ኅልውናም- መኖርም የምናየውና የምንግገነዘበው በፈጣሪያቸዉ ምክንያት -ስበብ አይደልለምን?

መንነሻና መጨረሻአልባው ፈጣሪ- አምላክ- መለኮት የሚትታዎቀውና የሚግገለፀውም በፍጥረታቱ ዓማካይነት ሲሆን ፍጥረታቱ ራሳቸዉ በጠ ቅላላም የፈጣሪያቸዉ መግገለጫዎችና ገፅታዎች- ዕይታዎች ናቸዉ። በመሆኑም ልክ እንደፈጣሪያቸዉ ሁሉ እነሱም ነበሩ- አልሉ -ይኖራሉ። ፍጥረት -ፍጡር ሁሉ ከፈጣሪው አይልለይምና ወይም ፍጡር ሁሉ ከፈጣሪው መልለየትና መንነጠል አይችልምና።

ካለመኖር ወደመኖር ማምጣት እና ከመኖር ወደአለመኖር መውሰድ የሚሉቱ ሐረጎች የሚያመለክቱት ግን ጥንተፍጥረትን ሳይሆን የቦታና ጊዜ ቅያሬንና ልውውጥን ብቻ ነው። መኖርና አለመኖም በጊዜና በቦታ ብቻ ይውወሰናል። ምክንያቱም መኖርና አለመኖር ለጊዜና ቦታ ወይም ለቦታ እና ጊዜ መሠረታዊ ባህርያቸዉ ነውና።

መኖር እና አለመኖር አንድ-ዋሕድ ናቸዉ ወይስ ሁለት ለሚለው ጥያቄም አዎንታና ዓሉታ ከሚሉቱ ሐረጎች ላይ በመጠኑ ያየነውን ክርክርና ጭቅጭቅ ያስነሣል ወይም ይቀሰቅሳል። ለእኛ እና በዚሁ ደረጃችን ግን መኖር እና አለመኖር ወይም አዎንታና ዓሉታ አንድ ነው የሚለውን ከያዝን በቂ ነው።

የኅልውናው መግገለጫ የሆኑቱ ፍጥረታትን ካለመኖር ወደመኖር ፈጣሪ -መለኮት- አምላክ ያመጣቸዉም ወይም በመጨረሻ የሚወስዳቸዉም በዓራቱ መሠረታዊ መደቦች ዓማካይነት ከፋፍሎ ነው። እነዚህም፣-

ሀ. ዓዜባዊው ነፋስ /ነፋስ ከዓዜብ/
ለ. ኮሬባዊው እሳት /እሳት ከኮሬብ/
ሐ. ናጌቫዊው ውሐ /ውሐ ከናጌቭ/
መ. ዱዳሌባዊው መሬት /መሬት ከዱዳሌብ/ ናቸዉ::

ለእነዚሁ መሠረታዊ መደቦችም ልክ እንደፍጥረታቱ ሁሉ የመርባት -መርራባቱ እና የመብዛት- መብባዛቱ ኃብትና ፀጋ ተሠጥቷቸዋል:: ምክንያቱም እነዚህም ፍጡራንና ፍጥረታት ወይም ለፈጣሪ መግገለጫዎቹ ናቸዉና::

ነፋስ እና ዓይነቶቹ ዓየር- እስትንፋስ የመሳሰሉቱ ሁሉ የሚርራቡት እነሆ በድንገትና ጭነት- ግፊት ዓማካይነት ነው::

እሳት እና የሙቀት ዓይነቶቹ ሁሉ የሚርራቡትና የሚብዛዙት ደግሞ በቅፅበት እና ግጭት ዓማካይነት ነው::

ውሐ እና የፈሳሽ ዓይነቶቹ በጠቅላላ የሚርራቡትና የሚብዛዙትም እንዲሁ በወቅትና ሂደት ዓማካይነት ነው::

መሬት እና የዓፈር-ጥጥር ዓይነቶቹ ሁሉ የሚብዛዙት ግን በሰዓት፣ ዕለታት፣ ሳምንታት፣ ወርኃት፣ ዓመታት እና ዘመናት ዓማካይነት ነው::

ከዚሁ በተጨመራሪም ከላይ የተጠቀሱቱ መደቦች ራስበራሳቸዉ እየተቀላቀሉና እየተዋሐዱ የሚሠጡት ውጤት ሲኖር ይህም ሕይዎት ያልለው /ሕይዎታማ/ እና ሕይዎትአልባ ተብሎ በሁለት መሠረታዊ መደቦች ዓማካይነት ይክከፋፈላል:: ሕይዎት ያልለው ሁሉ የሚርራባውና በሚብዛዛው በወንድዮሻዊና ሴትዮሻዊ ፆታ ግንኙነት ዓማካይነት ሲሆን ሕይዎትአልባው ለምሳሌ ደንጋይና የደንጋዩ ዓይነቶች ሁሉ በጠቅላላ የሚርራቡትና የሚብባዙት ደግሞ በዝገት እና ሥበት- መዘዝ- ማግኔት ዓማካይነት ነው::

እንደመላእክቱ፣ አጋዕዝቱና ኃይላቱ የመሳሰሉቱ ሁሉ ግን በጥንተ ተፈጠሯቸዉ ፍጹማን እና ምሉዓን በመሆናቸዉ ሕፀፅን -ጉድለትን -ግድፈትን- ቅናሴን- ሞትን እና ጭማሬን- ዕድገትን -ብዛትን- ልደትን መሠረት አድርጎ የሚድደረገውና የሚክከሄደው የመብዛት- መብዛዛት እና

የመርባት -መርራባት ሂደትና ተገብሮ ሁሉ እነሆ ለእነሱ ባህርያቸዉና ጥንተፈተጥሯቸዉ አይደልለም። ምክንያቱም እነሱ በባህርያቸዉ ዘለዓለማዉያን ናቸዉና። ወዘተ.

(ይበቃል- ይብቃን! ምክንያቱም ከዚሁ ላይ ወደባህርዩና ምንጩ ሐተታ ብንገባ ግን ይከብዳልና!)

በማለት አባቶቻችን አስተማሩን እንጅ የግሪካዉያኑ "ፈላስፋ" ፊደልቆጣሪዎች እና ቀንዕልጥራዝነጠቆች እንደሚቃዡት ሁሉ ፍጥረታት ከነፋስም ሆነ ከእሳት ወይም ከውሐም ሆነ ከመሬት እንዲሁ አልተነሡም። አለባለዚያም እንደዘመናችን ጭንቅላተቢሶች እና ግብዝደነዞች ሁሉ በጠቅላላ ራሳቸዉን በራሳቸዉ ፈጣሪ አድርገዉ አይቃዡምና አይባልጉም። ይልቁንም ይህንኑ ጥንታዊ ትምህርታቸዉንና ዕውቀታቸዉን ዐይተዉ ሌላሌላዎቹ ሁሉ በቀደም ጊዜ አማልክት እና የአማልክት ዘር እያሉ እነሱን ያከብሯቸዉና ያወድሷቸዉ ነበር እንጅ።

"ከዚያ ቦታ አማልክቱን በተመለከተ የተነገረኝን ሁሉ ግን ከዚሁ ቦታ ላይ ማካፈሉ ፈቃዴ -ፍላጎቴ አይደልለም። ምናልባትም ቢበዛቢበዛ ስማቸዉን ብቻ ከመጥራት በስተቀር። እንደእኔው ግንዛቤ ከሆነ የሰውልጆች ሁሉ በጠቅላላ አማልክቱን በተመለከተ የሚያውቁት- የተረዱት እጅግ በጣም ትንሽ- ቅንጣት- ኢምንት ነው። ይህንኑ በተመለከተ አሁን እኔው ራሴ ከዚሁ ላይ የዘገበኩበት ብቸኛው ምክንያቴም የታሪኩን- ትረካውን አንድምታ በበለጠ ለመርረዳት - ለመግገንዘብ ያስችላል በሚል ተስፋ ነው።"
(ሄሮዶት መጽሐፍ ሁለት ቁ. 3)

የእስካንዲናቢያ ዘላኖች ወይም የሳውድዓራቢያ ዘመናዊ "ወሐቢሴክቶች" ኢትዮጵያ ውስጥ እና ለኢትዮጵያዉያኑ እምነትንና ሃይማኖትን ሠብከውና አስተምረዉ አዎ "ጻድቃንና ቅዱሳን" ሊያደርጓቸዉ እየተጃጃሉ ነው፣ ብሎ ለሄሮዶት ቢያረዱት አብዶ ይሞት ነበረ!

-------------

(በነገራችን ላይ መጽሐፍ ቅዱስንም ሆነ ቅዱስ ቁርዓንን ብቻ አንብቦ ሥርዓተ እምነትን እና ሃይማኖትን ማወቅ አይችቻልም። ምክንያቱም እነዚህም ሆኑ የሌላሌላዎቹ አማኞች ቅዱሳት

መጻሕፍት ሁሉ መምመሪያ ናቸዉ እንጅ የሃይማኖቱ እና እምነቱ ቀኖና ግን ፈጽሞ- በፍጹም አይደሉምና። የአማኞቹ መምመሪያዎች እንጅ የሃይማኖቱ ቀኖና ናቸዉ ብሎ የሚያስተምረው ሁሉ አንድም አላዋቂ ነው ወይም እምነታዊ ቀኖናን አያውቅም አለባለዚያም ሁን-ሆን ብሎ ሰዎቹን ያታልላል፣ ማለት ነው። እንደዚህ ብሎ ማስተማሩም ቢሆን ድፍረትና ብልግና ነው። "መጽሐፍ ቅዱስን አንብብና ክርስቲያን ሁን-ይትሆናለህ!" እየተባለ በኢትዮጵያዉያኑ አማኞችና ምእመናኖች ላይ ዛሬ የሚፍፈጸመው ግፍበደል ሁሉ ጥርት ያለ ወንጀል ነው።)

---